# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 21

ሰኔ 5 ቀን 2014 ዓም(12-06-2022)

የአገራችን ሰሞንኛ ጉዞ በብዙ ውስብስብ ችግሮች፣እንቅፋቶችና ጋሬጣዎች የተተበተበ ሲሆን የሁሉም አይነት ቀውስና ችግር ባለቤቱ በጎሳ ማንነት የተሰባሰበውና ሥልጣኑን በጉልበት የተቆጣጠረው መንግሥት ነኝ ባይ ቡድንና በዓላማ የማይለያዩት ግን በሥልጣን ሽኩቻ እርስ በርሳቸው የሚባሉት አገር ጠል የሆኑ ቡድኖች ናቸው።

ደግመን ደጋግመን እንዳሳሰብነው የነዚህ ቀደም ሲል በኢሕአዴግ አሁንም በብልጽግና በሚል ካባ ተጠቅልለው ሥልጣኑን በተቆጣጠሩ ጸረ ኢትዮጵያ ስብስቦች ፣በከተማም ሆነ በጫካ የሚርመሰመሱና በፓርቲ ስም የመንግሥት እውቅና የተቸራቸው ቡድኖች ካልጠፉ ችግርና መከራው ብሎም የአገር መበታተኑ አደጋ ሊወገድ አይችልም።የዝሆኖች ግብግብ ለሳሩ ይተርፋል እንደሚባለው የነሱ የሥልጣንና የጥቅም ግብግብ ጉዳቱ ለሕዝቡና ለአገሪቱ ይተርፋል። በአንድ አገር ልጅነት ተቀራርቦና ተግባብቶ ብሎም ተዋልዶ የኖረውን ሕዝብ ፣በቋንቋና በእምነቱ፣በነጠላ ጎሰኛ አስተሳሰብ የፍጥኝ ቀፍድደው ይዘው እርስ በርሱ እንዲጋጭና እንዲጋደል፣በጠላትነት እንዲተያይ የሚያደርጉት እነዚሁ በስም እንጂ በዓላማ የማይለያዩ ከዘመኑ አስተሳሰብ ጋር የተጣሉ በ21ኛው ክፍለዘመን የ16ኛውን ክፍለዘመን ህሳቤ የተሸከሙና ተግባራዊ ለማድረግ የሚሯሯጡ የሚለያያቸው ቢኖር ዓላማቸውን ለማስፈጸም በትረመንግሥቱን የመጨበጥ ፍላጎት እንጂ የዓላማ ልዩነት እንደሌላቸው ደግመው ደጋግመው በተግባር አሳይተዋል።አሁንም እያሳዩ ነው።አገር ከመበታተኑ ጋር የተያያዘው ፍላጎታቸው ደግሞ ገንጥለው የሚፈጥሩትን ቦታ አገር አድርገው ሕዝቡንም ሃብቱንም የግል ይዞታና መጠቀሚያ ለማድረግ ነው።አሁንም ክልል ብለው በፈጠሩት አገራዊ ግዛት በስልጣን ላይ የተቀመጡት ሰዎች የያዙትን የዘረፋ ዕድል ላለማጣት ተባብረው የሕዝቡን የለውጥ ጥያቄ እያፈኑ፣ተቃዋሚና የማህበረሰብ አንቂ ናቸው የሚሏቸውን ለእውነትና ለሕዝብ መብት የሚከራከሩ፣የሚጠይቁና የሚያጋልጡ ጋዜጠኞችን፣ፖለቲከኞችን፣የሃይማኖት መሪዎችን፣ባለሙያዎችን፣የመንግሥት ሠራተኞችን፣የመከላከያ አባላት ሳይቀሩ በመግደል በማሠርና በማሳደድ ተግባር ላይ ተሰማርተዋል።

ይህንን እኩይ ተግባር ለማሳዬት የሚከተሉትን ጥቂት ድርጊቶች በዋቢነት እናቀርባለን።

የኢትዮጵያን እንደ አገር ለማስቀጠል የጎሰኞችን አስተሳሰብና አካሄድ ያልተቀበለው፣ለዘመናት የኢትዮጵያ ጋሻና መከታ ሆኖ የኖረውን የአማራ ማህበረሰብ ለማሽማቀቅና ለማሳነስ ብሎም ሞራላዊ ና ወታደራዊ ትጥቁን ለማስፈታት ሁለገብ ዘመቻ እዬተደረገበት መሆኑ ይታወቃል።የዚሁ የጎሰኞች ስርዓት አካል የሆነው በአማራ ስም አጥር ሰርቶ ሥልጣን ላይ የተቀመጠው፣የአማራውን አንገት ለማስደፋት በአማራው አንገት ላይ የተንጠለጠለ የብረት አሎሎ፣በእግሩ ላይ የተተበተበ እግረሙቅ ወይም እግርብረት የሆነ ብአዴን የተባለው የሌባ ስብስብ በተረኝነት በትረመንግሥቱን የጨበጠው የኦሮሙማው አነግ ኦሕዴድ ቡድን ለሚያካሂደው የማጥቃት ዘመቻ ሎሌና ጠቋሚ በመሆን የብዙ ዜጎች ህይወት አስጠፍቷል፣ንብረት አውድሟል፣ቤተሰብ በትኗል።ሕዝባዊ ሃይል የሆነውን የፋኖን መሪዎችና አባላት እንዲሁም ቤተሰቦች በማሳደድ ታማኝነቱን ገልጿል፣እዬገለጸም ነው። እጁን በእጁ እዬቆረጠ መብላት የማይሰለቸውና የማይመረው ይህ ቡድን ከጸረ አማራ ፣ከጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎች ጋር ጥምረት ፈጥሮ ባልታጠቁ በሰላማዊ ታጋዮች ላይም የማሳደድና የማሰር ዘመቻውን በግንባር ቀደምትነት እዬመራው ይገኛል።

ሃሳብን እንደ ቦምብ ብዕርን እንደሚሳይል የሚፈራው የኦሮሙማ ተረኛ መራሹ ስብስብ ጋዜጠኞችንና ተችዎችን በማሰርና በማሳደድ በራሱ የካንጋሮ ፍርድ ቤት አቅርቦ ቅጣት እዬበየነባቸው ይገኛል። ሌሎቹንም በዚሁ ፍርድ ቤት ሳያቀርብ በጨለማ ቤት አጉሮ በማሰቃዬት ላይ ነው።ካንጋሮ እስር ቤት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቅና የሚወገዝ በፍትሕ ላይ የሚቀልድ የፍርደገምድሎች መድረክ ሲሆን ሌላው ዓለም በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል።"Kangaroo courts are systems that are set up to give the illusion of a fair and just legal process, when in actuality they do not support unbiased justic.Instead ,they often decide the fate of the accused in advance ,usually for the purpose of securing a conviction"ይህ በአማርኛ ሲተረጎም ካንጋሮ ፍርድ ቤት የተከሳሽን ቃልና መከራከሪያ ምላሽ ሳያዳምጡና ከመጤፍ ሳይቆጥሩ በተከሳሹ ላይ ሊቀመጥ የሚችለውን ቅጣትና ፍርድ አስቀድሞ አዘጋጅተው የሚመጡበት ተከሳሹን የሚጎዱበት ከሳሹን የሚያገለግሉበት ለይምሰል የሚሰይሙት የፍርድ ሂደት ነው።ይህ ማለት ከሳሹ መንግሥት ሊረታና ተከሳሹን በሚፈልገው መንገድ ሊቀጣበት የሚችል የፍርደ ገምድል አሠራር የሚጸድቅበት ለህሊናቸውና ለሙያው የቆሙ ዳኞች ሳይሆኑ ለጥቅም ያደሩ ጥቁር ካባ የለበሱ ምንደኞች የሚሰዬሙበት ችሎት ማለት ነው።በዚህ አይነቱ ችሎት ብዙ ንጹህ ዜጎች ለስቃይና ለመከራ ተዳርገዋል፤በመዳረግም ላይ ናቸው።በእኛም አተረጓጎም ካንጋሮ ልጇን የምትደብቅበትና ይዛ የምትሮጥበት ከሆዷ ስር የተለጠፈ ኪስ ወይም ቦርሳ እንዳላት ሁሉ ምንደኛ ዳኞች የሚወክሉትን ስርዓት ለማዳን የሚችሉበትን፣ተቃዋሚውን የሚጎዱበትን ውሳኔ በቅድሚያ አዘጋጅተው እንደ ካንጋሮዋ በኪሳቸው ይዘው የሚመጡበትን ሁኔታ ይገልጻል ብለን እናምናለን።

ከሃያ በላይ የሚሆኑ ጋዜጠኞችና የማህበረሰብ አንቂዎች፣ፖለቲከኞችና ተቃዋሚ ሙያተኞች እዬታፈሱ የሚቀርቡት በዚሁ የካንጋሮ ችሎት ፊት ነው።ፈጽመዋል ለተባለው ወንጀል ምንም ማስረጃ ሳይገኝባቸው ታድነው የሚያዙት ከህብረተሰቡ ነጥለን ተቃውሞውን እናሶግዳለን ወይም እናበርዳለን በሚል ስንኩል ምኞት ቢሆንም የተከሳሾቹ ሞራልም ሆነ ቅስም ሊሰበር አልቻለም።የሕዝቡም ተቃውሞ ይበልጥ ተጠናከረ እንጂ እዬቀነሰ አልመጣም። አንድ ፋኖ ሲገሉ በሙቶ የሚቆጠር ፋኖ ጫካ እዬገባ ነው።አንድ ጋዜጠኛና ተቃዋሚ ሲያስሩ አስርታት ጋዜጠኞችና ደጋፊዎች እዬፈለቁ ነው።በዚህ ግራ የተጋባው መንግሥት ነኝ ባይ ቡድን ካፈርኩ አይመልሰኝ ብሎ ሕዝቡን ለማጭበርበር በገንዘብ ዋስትና ለመልቀቅ ለዳኞቹ ትዕዛዝ ቢሰጥም በሌላው እጁ በሆነው በፖሊስ በኩል ምክንያት እዬፈለገ የካንጋሮ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በመጣስ ግፉአንን ለተራዘመ ጊዜ ለማሰቃዬት በክስ ላይ ክስ እዬመሰረተ በፍትሕ ላይ ይቀልዳል።መቀለድም ብቻ ሳይሆን ፍትሕን በዱላ እዬጠለዘው ይገኛል።

አባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ ሆነና ፖሊስና ፍርድ ቤቱ እጅና ጓንት ሆነው የፈረደበትን ሕዝብ እዬተቀባበሉ አበሳ በማሳዬት ላይ ናቸው። ቀደም ሲል ፍርድ ቤት በገንዘብ ዋስትና ይፈታ ያለውን ልደቱ አያሌውን የኦሮሙማው ፖሊስ አለቅም ብሎ ለወራት እንዳጉላላው ሁሉ ሰሞኑን ደግሞ በገንዘብ ዋስትና ይለቀቁ ብሎ የፈረደባቸውንና ገንዘቡን የከፈሉትን ጋዜጠኞች መአዛ ሞሃመድን፣ሰለሞን ሹምዬንና ተመስገን ደሳለኝን ፖሊስ አለቅም በማለት ለሌላ ክስ እዬተዘጋጀ መሆኑ ተሰምቷል።እንደዚህ የሕግ ወይም የፍትሕ ሥርዓት ሲጣስና ትርጉመ ቢስ ሲሆን ፍትሕ በፖሊስ ዱላ ሲደበደብ ሕግ አውጭው አካል የሆነው ምክርቤት (ፓርላማ) ድምጹን አለማሰማቱ ዱሮም ቢሆን ካልነበረው ከሕዝብ ምክርቤትነት ተርታ ያሶጣዋል።ከስህተቱ ቢማርማ ኖሮ ያወጣሁት ሕግ በደምቡ አልተተረጎመም በአግባቡም አልተፈጸመም ብሎ በመንግሥት ላይ ተቃውሞ ባሰማ ነበር።

ለመሪዎቹና ለፖለቲካቸው ውጋትና መቅሰፍት የሆነችው፣በክርክርና በእውቀትና በማስረጃ ላይ በተመሠረተ ትችት የሥርዓቱን ምንነት የምታጋልጠው መስከረም አበራም እንዲሁ ከሚጠባ ልጇ

ተነጥላ በቁጥጥር ስር ውላ የፍርድ ያለህ ትላለች።በእሷ ላይ የቀረበውማ ክስ ባለሥልጣኖችን አሸብራለች፣እንቅልፍ ነስታለች በሚለው ክስ ላይ የሁለት መቶ የኬንያ ሽልንግ ፣ሲመነዘር አርባ የኢትዮጵያ ብር በቦርሰዋ ይዛለች የሚል የሚያስቅና የሚያስገምት ክስ መቅረቡ ነው።ብዕርና ወረቀት የሚያሸብራቸው ባለሥልጣኖችና የጦር አለቆች እንዴት አድርገው የጠላትን የጦር መሣሪያ፣ቦምብና፣ መድፍ ፣ታንክና ፣አውሮፕላን እንደሚቋቋሙት ሲያስቡት አያድርስ ያሰኛል። ግን ጠላት በዋለበት የጦር ሜዳ ላይ ስለማይገኙ ለዚህ ይጋለጣሉ ተብሎ አይጠበቅም።

ባልደራስ  ለእውነተኛ ዴሞክራሲ የሚባለው የፖለቲካ ድርጅት አንዱ መሪና ጋዜጠኛ ስንታዬሁ ቸኮልም በጨለማ ቤት ታጉሮ ፣ለካንጋሮ ፍርድ ቤት እንኳን ሳይቀርብ ለበሽታና ለእንግልት ተዳርጎ ከሰነበተ ውሎ አድሯል።ሌሎቹም በተቃዋሚ ጎራ ያሉት የሕዝብ ልጆች በያቅጣጫው ግፍና በደል እዬተፈጸመባቸው ይገኛል።ይህንን ሁሉ ግፍና በደል በአገር ውስጥና በውጭ አገር የሚኖረው አገር ወዳድ መንግሥት ነኝ ባዩን የጎሰኞች አገር አጥፊ ቡድን እያጋለጠውና እየተቃወመው ይገኛል።በዚህም የተነሳ  በአገዛዙ ጎራ መደናበርና መባላት በግልጽ እዬታዬ መጥቷል። ያልወድቅ ባይ ተጋዳይ ዘመቻውን ፣የአስገዳጅ አዋጁን እያዝጎደጎደው ይገኛል።ሆድ አደር ጋዜጠኛ ደጋፊዎቹም እሪታቸውን እያቀለጡት ነው።በእነሱም በኩል ቢሆን የመረበሽና የመዋዠቅ አቋም እዬታዬ መጥቷል።ሽንጣቸውን ገትረው ለመንግሥት ጥብቅና ቆመው ሕዝቡን ሲያወናብዱና ተቃዋሚውን ሲያወግዙ የነበሩ ጋዜጠኞች በመንግሥት ላይ ተነስተዋል።አንዱ መሳይ መኮንን የተባለው የሥርዓቱ ደጋፊ የመንግሥት ተደጋጋሚና አሰልች ውሸት ቋቅ አለኝ ሲል ሌላው ስዩም ተሾመ የተባለው ሽንጤን ገትሬ የተከራከርኩለትና የደገፍኩት መንግሥት አዋረደኝ፣አጋለጠኝ፣ፍትሕን እዬጣሰ ንጹሃንን ማሰሩና ማሳደዱ፣ፍርድ ቤቱና ፖሊሱ በተቃርኖ መቆማቸው እንቅልፍ ነሳኝ፣ባለጌና ዘረኛ ስርዓት መሆኑ አሁን  በግልጽ ቦግ ብሎ ታዬኝ፤ከአሁን በኋላ መስመሩን ካላስተካከለ ለዚህ መንግሥት አልቆምም ሲል የምሬት ቃሉን አሰምቷል።እነዚህና እነዚህን የመሰሉት ከጊዜውና ከሁኔታው ጋር የሚነፍሱ በመሆናቸው በያዙት አቋም ይቀጥላሉ ብሎ ማመን ባይቻልም የሰጡት ምስክርነት ለተቃዋሚው ጎራ ሃቀኝነት ማረጋገጫ ይሆናል።የማሸነፉም ምልክት ነው።አልሸሹም ዘወር አሉ እንዲሉ መሳይ መኮንን ተቃውሞውን የቋጨበት ቃል በሥርዓቱ ላይ እምነት እንዳለውና አሁንም በምክር ይሻሻላል፣ መሪውም አብይ አህመድ ለውጡን ያሳካሉ የሚል እምነት አለኝ ሲል ትችቱን ደምድሟል።በእኛ እይታና ግንዛቤ ሥርዓቱን ከመሪው ነጥሎ ማዬት የሸውራራ  እይታ ከመሆን ያለፈ ከልብ የመነጨ እውነተኛ መጸጸትና ተቃውሞ አይደለም እንላለን።

የሕዝብ ትግል እያደገ ሲመጣ አይተነው ጊዜ በሚል የብልጣብልጦች የሰልፍ አዝማሚያ መኖሩ አይካድም።ካሁን በኋላ ግን የብልጣብልጦች መስሎ ማደር ካርታው አርጅቷል።ሊጫወቱበት አይችሉም።ያላቸው ዕድል እስከአሁን ድረስ ያደረሱትን ጥፋት አምነው በግልጽ ዘርዝረው በማቅረብ ላደረሱት ጥፋት ተጸጽተውና ንስሃ ገብተው፣ሕዝቡን ይቅርታ ጠይቀው ከፖለቲካው መድረክ ተገልለው ከህሊና ቁስል ለማገገም ሱባኤ መግባት ብቻ ነው።

በብልጽግና ተብዬው ስብስብ ውስጥ የእርስበርስ ሽኩቻውና መባላቱ፣እዬከረረ የመጣበት ጊዜ  ላይ ደርሰናል።ግማሹ የተቃዋሚውን ጎራ ሲቀላቀል ከፊሉ በፍርሃት ተርበድብዶ የሚኖርበትን ቦታ እዬለቀቀ ለመሄድ ተገዷል።በጎሳ መስክ ላይ የተዘራው ሥርዓትና ተቋም እዬፈራረሰ በመሄድ ላይ ነው።የእምቧይ ካብ ሆኗል።

በእውር ድንብሩ የሚኳትነው መንግሥት በአማራው ላይ ተጨማሪ ጦር አሰማርቷል።ሕዝብንም በማስገደድ ከጎኑ እንዲቆም እያደረገ ነው።ከሚወስደው የሃይል እርምጃ በተጨማሪ ማግኘት የሚገባውን መብቱን እዬነፈገ የድጋፍ መሰብሰቢያ አድርጎታል።ለገበሬው የማዳበሪያ፣ለተቸገረው ነዋሪ

የድጎማ እርዳታ(Safty Net)አገልግሎት በመንፈግ በችግር አስገዳጅነት ከጎኑ እንዲቆም ለማድረግ መመሪያ አውጥቶ በመንቀሳቀስ ላይ ነው። ያልቻለው እጁን ሲሰጥ ብዙሃኑ ግን አሻፈረኝ ብሏል፣ ለጊዜው በሆዱ ገዛነው ብለው ቢያስቡም ልቡን ሊገዙት አልቻሉም፣አምጿል።በፍኖተ ሰላም የድጋፍ ሰልፍ እንዲወጣ የተደረገው ሙከራም የከሸፈው በዚሁ ሕዝባዊ እምቢባይነት ምክንያት ነው። በኦሮሙማው መዳፍ ስር የወደቁት የከሚሴ ፣የሰንበቴና የባቲ ነዋሪ የኦሮሞ ጎሳ ተወላጆች ብቻ የድጋፍ ሰልፍ አድርገዋል።በትግል ወቅት ተቃዋሚ እንዳለ ሁሉ ደጋፊም መኖሩ ስለማይካድ የጥቂቶቹ ከሥርዓቱ ጋር መቆም የሚያስገርም አይሆንም።ትግሉ በአገር ወዳዶችና በአገር ጠሌዎች መካከል እስከሆነ ድረስ በዚያ ካምፕ ወይም ጎራ የሚሰለፉ መኖራቸው አይካድም።የማታ ማታ የድሉ ባለቤት የሚሆነው ግን እውነትንና፣አብሮነትን፣ሊጋራ ጥቅምና እኩልነት፣ ለዴሞክራሲና፣ከመንደር ምስለኔነት ይልቅ ለኢትዮጵያ አገራዊ ባለቤትነት የሚታገል ሕዝብ እንደሆነ ቅንጣት አያጠራጥርም፤በታሪክም ታይቷል።

ይኸው አገር ጠሌው የኦሮሙማው መንፈስ አገር ብቻ ሳይሆን የራሱንም ጤና የሚጠላ መሆኑን በአርሲ የሚገኙትን ሃኪሞች መቆሚያ መቀመጫ ማሳጣቱና ለሚጠይቁት ዴሞክራሲያዊ ጥያቄ መልስ ሳይሰጥ በዱላና በጉልበት ለማንበርከክ መወሰኑ ነው።በዚህ የኑሮ ውድነት በሰፈነበት፣ከእጅ ወደአፍ ለሆነች፣ከአንድ በግ መግዣ ለማታልፍ ደመወዝ የወገናቸውን፣የሰው ልጆችን ጤንነት ለመንከባከብ እራሳቸውን መስዋእት የሚያደርጉ ሃኪሞችን ማክበርና መንከባከብ ሲገባ ማሰቃዬት አንድም ከያዙት ጠባብና ኋላ ቀር እምነት ሌላም ከምቀኝነት ከመነጨ እርኩስ ሃሳብ እንጂ ከአስተዋይነትና ከሕዝባዊነት አይደለም።በዛፍ፣በወንዝና በተራራ፣በአባይ-ጠንቋይና በአቴቴ ግንቦቴ የሚያምን ማህበረሰብ ለዘመናዊ ሕክምና በር ይከፍታል ብሎ መጠበቅ ሞኝነት ነው።ከዚሁ ከአርሲ ሳንወጣ  ከነበሩበት የካሪቢያን አገር ከጃማይካ መጥተው ኢትዮጵያን አገራችን ብለው፣ማንንም ሳይነኩና ሳይጎዱ በሰላም የሚኖሩ፣ሰንደቅ ዓላማዋን በዓለም ደረጃ እያውለበለቡ ያስተዋወቁ ራስ ተፈሪያን በመባል የሚታወቁ ኢትዮጵያውያንን በምቀኝነትና በጸረ ኢትዮጵያዊነት ልክፍት የተለከፈው የኦሮሙማው ቡድን ከኖሩበት የሻሸመኒ ከተማ እንዲለቁ ንብረታቸውንና መብታቸውን በመግፈፍ ላይ ነው።ከሞት የተረፉት ወደ አዲስ አበባ ሲገቡ የቀሩት ኢትዮጵያን ለቀው በመሰደድ ላይ ናቸው።ጥለውት ለሄዱበት አገር ለጃማይካ መሬት የሚበቁት ጥቂቶች ናቸው።የነዚህ ሰላማዊ ሰዎች ጥፋት የሆነባቸው ኢትዮጵያንና ሰንደቅ ዓላማዋን መውደዳቸው ብቻ ነው።

የእኩይ አምልኮን ካነሳን አይቀር ከሰሞኑ የታዘብነውን መጨመሩ ትችታችንን እውነትና የተሟላ ያደርገዋል።የኦሕዴድ-ኦነግ ብልጽግና መሪ የሆነው አብይ አህመድ ብርቱካን ከተባለች በፕሮቴስታንት እምነት ስም ነብይ ተብላ ከተገሸረች ጠንቋይ ጋር ባደረገው ምስጢራዊ የስልክ ግንኙነት አምላክ ተቃዋሚህን ፍለጠው፣ቁረጠው፣ጭንቅላቱን ቀጥቅጠው ፣አትፍራ! አትራራ! ከጎንህ ነኝ ብሎሃል ስትል የሰማነው ከህሊናችን ሳይጠፋ ከቀናት በፊት የፖሊሱን ምርቃት ለማክበር በቦሌ ድልድይ ሥር በተካሄደው ዝግጅት ከድልድዩ ሥር ጥራጥሬ የመልቀም ልማድ ያላት እርግብ እንደለመደችው በራ በእለቱ አብይ በተቀመጠበት አጠገብ በማረፏ ከአምላክ የድጋፍ መልእክት ይዛ እንደመጣች ተደርጎ በሆዳም ጋዜጠኞችና የወሬ አራጋቢዎች የተሰራጨው በሬ ወለደ ምን ያህል ሥርዓቱና መሪው በድግምትና በጥንቆላ ሕዝቡን ለማሳሳት እንደሚሞክር ማሳያ ነው።ገና ከጅምሩም ሰባተኛ ንጉሥ ትሆናለህ ተብያለው ብሎ ማለቱ ከጥንቆላ ጋር ያለውን ትስስር አመላካች ነው።

የአብይ አህመድ መንግሥት ከቀድሞ አለቆቹ ከወያኔ ባለሥልጣኖች ጋር ለመስማማት ተደጋጋሚ ግንኙነቶችና ውይይቶች ማድረጉ የአደባባይ ምስጢር ከሆነ ሰንበቷል።ስምምነቱን ለመቋጨት ዳር ላይ እንደደረሱም የሚወጡት መረጃዎች ያመለክታሉ።የስምምነቱ መቋጫም የወልቃይትና የራያ ለም

መሬትን ለወያኔ አሳልፎ መስጠቱ እንደሚሆን በከባቢው በሚኖረው የአማራ ሕዝብ ላይ የሚካሄደው መንግሥታዊ አሻጥርና ተጽእኖ ያረጋግጣል።ወያኔም በሃይሌ የወሰድኩት ነው ለማለትና የመንግሥትን ተባባሪነት ለመሸፋፈን ለዳግም ወረራ በመዘጋጀትና አልፎ አልፎም ውጊያ በማካሄድ ላይ ተሰማርቷል። ለወያኔ የሚፈልገውን ሰጥቶ ኦነግ-ኦሕዴድ  የሚፈልገውን ለመውሰድ የጋራ ስምምነት አድርገዋል። በሁለት ጣምራ ጠላቶች የተከበበው የአማራው ማህበረሰብ በውስጡ ባሉት አድርባዮች የሚደርስበት ክህደት በቀላሉ የሚታይ አይደለም።በጎጥና በሃይማኖት ለያይቶ ሃይሉን ለማዳከም የሚሸረበው ሴራ አልቆመም።በማሰርና በማሳደድ የታጀበው ጥቃት የሚፈጸመው በነዚሁ የውስጥ አርበኞች ተባባሪነት ነው።አገር ወዳዱ ሕዝባዊ ሃይል በነዚህ ላይ መረር ያለ እርምጃ መውሰድ እንዳለበት በዚህ ምክር አዘል ነባር ስንኝ ልናሳስብ እንወዳለን።

ጠላትማ ምንጊዜም ጠላት ነው፤

አስቀድሞ መምታት አሾክሿኪውን ነው፣

ባንዳ አድር ባዩን ነው።!

ጭቅጭቅና ንትርኩ በጸረ አንድነቱ የጎሰኞች ጎራም በተለይም በኦሮሞ የኦነግና  የኦፌኮ ድርጅቶች መካከል ያዬንበት ሰሞን ነው።እነዚህ ኢትዮጵያን በማፍረስ የሚስማሙ ግን እንመሠርታታለን ብለው በሚያስቧት ኦሮሚያ በተባለች የቅዠት አገር ላይ በሚነሳው የሥልጣን ድርሻ መናቆራቸው የሚታወቅና የቆዬ መሆኑ አይካድም።ያንን የቆዬ ልዩነት በባንዲራ ምክንያት አድርገው ሲነታረኩበት ታዝበናል። ባንዲራ የዬድርጅቱን ዓላማና አሰላለፍ ገላጭ በመሆኑ የኦነግና የኦፌኮ በባንዲራው  መነታረካቸው የዚያው ነጸብራቅ እንጂ የዓላማ ልዮነት ኖሯቸው አይደለም።ዳውድ ኢብሳ ተሸክሞት የኖረውን ባንዲራ አሁን የኦፌኮው ጁዋር ሙሃመድ ተሸክሞ በዬስብሰባው ላይ መታዬቱ ስጋት ያደረበትን ኦነግን በኦፌኮ ላይ ተቃውሞ እንዲያነሳ አድርጎታል።ይህ ንትርካቸው ለኢትዮጵያ የተሻለ ነገር በመፍጠሩ ዙሪያ እንዳልሆነ ቢታመንም በጠላቶች ጎራ የሚነሳ ጭቅጭቅና ውዝግብ ብሎም ግጭት እንዲፋፋም ማድረጉ ተገቢ ይሆናል።ሌላው ቢቀር የጠላት ጎራ ሲታመስ የአገር ወዳዱ ጎራ እንዲጠናከር ዕድልና ፋታ ይሰጠዋል።ስለሆነም ከነዚህ ጠላቶቹ ጠብ የሚል በጎ ነገር ይኖራል ብሎ ሳይዘናጋ የራሱን የቤት ሥራ መሥራቱ ተገቢ ነው እንላለን።

የኸው የፖለቲካ ወጠጤ ጁዋር ሞሃመድ እራሱን እንደ ተራራ አሳብጦ የእርቅና የሰላም አባት ሆኖ ለመቅረብ ሞክሯል።ወያኔን፣ሸኔንና የጉምዝ ታጣቂዎችን ለማስማማት በሽምግልና ለመጫወት ያለውን ፍላጎት ገልጿል።ቢሳካለት ተባብራችሁ የጋራ ጠላታችንን አማራውንና ኢትዮጵያዊነትን እናጥቃ ለማለት ነው።ይሉሽን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ ከማለት ያለፈ ለዚህ ወስላታ ትኩረት በመስጠት ጊዜያችንን አናባክንም።ሆኖም ግን በውጭ አገር በተለይም በአውሮፓ በፈረንሳይ፣በስዊድን፤በጀርመንና በሌሎቹም ከተማዎች እዬዞረ ተከታዮቹን በመሰብሰብ ኢትዮጵያን በማፈራረሱ ደባ ላይ እዬሠራ መሆኑን ማሳወቅ ተገቢ ሆኖ አገኝተነዋል።የጁዋርና የሌሎቹ እንቅስቃሴዎች ከጀርባቸው የምዕራቡ በተለይም የአሜሪካኖች ድጋፍና እውቅና እንዳለው መጠርጠሩ የጠላትን ካምፕ አሰላለፍ እንድናውቅ ይረዳናል። በአገር ቤት የ10 ተቃዋሚ  ነን ባይ ድርጅቶች ኦነግ፣ኦፌኮንና ሌሎቹን ጨምሮ በአሜሪካ ኤምባሲ ግቢ መመርመሳቸውና የሽግግር መንግሥት ይቋቋም ጥያቄ፣ከዚሁ የጎሰኞች ሴራና የውጭ ሃይሎች መተጋገዝ ውጭ  እንዲታይ አያደርገውም።ይህንን የተቀናጀ እንቅስቃሴ ከተባበሩት ኢሚራት በአባይ ግድብ የውይይት ጣልቃ ገብነት ፍላጎት ጋር ስናስተሳስረው የጸረ ኢትዮጵያ ጎራው ምን ያህል እዬሰፋ መምጣቱን እንረዳለን።

ዕድሜ ለአብይ አህመድ እንበልና ኢትዮጵያን ያህል ትልቅ ታሪካዊ አገር በኢሚራቶችና በሌሎቹ መዳፍ ሥር እንድትወድቅ ያደረጋት የሱ መርመጥመጥና ለዝናና ለጥቅሙ በር መክፈቱ ነው።ሌላው ቀርቶ የጅቡቲና የኬንያ መጫወቻ ለመሆን የበቃችው ፣በአገርነት ሳትታወቅ ለዓመታት የቆዬችው የኢትዮጵያ ጥንታዊት የባሕር በር የነበረችው የበርበራ ግዛት መሪዎችም እንዳሻቸው የሚፈነጩትና ፣በቅርቡ በስምምነት ያገኘችውን የወደብ ሽርክናና ባለቤትነት ለመሰረዝ የበቁት ወደቡን በማልማትና በመቆጣጠር ከፍተኛ ድርሻ የያዘችው በተባበሩት ኢሚራት ግፊት ሊሆን እንደሚችል ከሂደቱ መረዳት ያስችላል።ኢሚራቶች ገለልተኛ በመምሰል ኢትዮጵያ ያልከፈለችውን የወደብ ግንባታ ገንዘብ እሰጣለሁ በሚል ሽፋን አድራጊ ፈጣሪነቷን ለማሳዬትና የግድቡን ስምምነት ግብጽና አሜሪካ በሚፈልጉት ደረጃ ለማስኬድ ልትጠቀምበት የምትችልበት ስልት እንደሆነ መጠርጠሩ ብልህነት ነው።አብይ አህመድ ገንዘብና እውቅና ከሰጡት ስለአገር ክብርና ልዑላዊነት ደንታው አይደለም።የቀረውንም አሳልፎ የሚሰጥ ከሃዲ መሆኑን በኢሳያስ አፈወርቂ ላይ የፈጸመው ክህደት በቂ ማሳያ ነው።እባብ ለባብ ይተያያል ካብ ለካብ እንዲሉ ሁለቱም እንጠቀማለን ባሉበት የፖለቲካ ጋብቻ ሳይገፉበት ለመቃቃር በቅተዋል።ሕዝቡ ከዚህ ሊማር የሚችለው ቢኖር ሕዝብ ለሕዝብ ተወያይቶና ተነጋግሮ የሚፈጥረው የጋራ መፍትሔ ከሌለ በስተቀር በመሪዎቹ መቀራረብና ፍላጎት ብቻ ጥያቄው ሊመለስለት፣ሰላሙ ሊረጋገጥለት፣እድገቱና ፍትሕ ሊሰፍንለት እንደማይችል ነው።መሪዎች ሲጣሉ የሚያጣሉት፣ሲቀራረቡ የሚያቀራርቡት መጫወቻ ይሆናል ማለት ነው።ይህ መቀጠል የለበትም፤ሕዝቡ በቃ ሊል ይገባል።

ለኢትዮጵያ የሚያዋጣት የባሕር በር ከኤርትራ የተሻለ ሊኖራት አይችልም ብለን እናምናለን።ሕዝብ ለሕዝብ በሚያደርገው ውይይትና መቀራረብ በውጭና በውስጥ ሴረኞች የተተበተበውን የልዩነት ገመድ በጣጥሶ ፣የጠላትነት ድባቡን ገፎ በጥምረት (ፌዴራል) ስርዓት ዘርግተው ለመኖር ለዘመናት የነበራቸው፣ታሪካዊ፣ማህበረሰባዊና ባህላዊ፣ሃይማኖታዊና ኤኮኖሚያዊ፤ብሎም በኩታገጠም መሬት ባሳለፉት ኑሯቸው ያተረፉት መስተጋብር ለሁለቱም አገር ሕዝቦች የዘለቄታ እድገትና ሰላም ቁልፍ ነው ብለን እናምናለን።የነሱ መተሳሰር ለቀረው የምስራቅ አፍሪካ ሰላምና እድገት ብሎም ነጻነትና መከበር ወሳኝነት አለው።የትግራይ ልሂቃንም ከወያኔ ሰይጣናዊ አስተሳሰብ ወጥተው የጥንታዊት ኢትዮጵያዊነትን ማንነት ተላብሰው አብረው ከኖሩትና ከተዋለዱት ሕዝብ ጋር እንደዱሮው ለመኖር በሚያስችለው ቁመና ላይ እንዲገኙ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።የሁሉም ኢትዮጵያውያን በሆነችው አገርና መሬት ሁሉም በነጻነት ሠርቶ የመኖርና ሃብት የማፍራት መብቱ በሚከበርበት ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በማስፈኑ የጋራ ትግል ውስጥ መሰለፉ ለታሪክም ለትውልድም የሚያኮራ ተግባር መሆኑን እንዲገነዘቡት ለማሳሰብ እንወዳለን።ከሰላሳ ሁለት ዓመት በፊትም ሕዝቡ አብሮ መኖሩን ልብ ሊሉት ይገባል።ሁሉም ሥርዓቱ እንዲቀዬር እንጂ ዜግነቱን ለመቀዬር፣በቁራሽ መሬት ጭቅጭቅ የገባበትና የታገለበት ጊዜና ታሪክ አልነበረም።አሁንም የሕዝቡ ፍላጎት በሰላምና በመከባበር አብሮ መኖር ነው። የተገነጠለውም ሆነ እንገንጥልህ የሚሉት ሕዝብ በመገንጠል ያገኘውና የሚያገኘው ጥቅም እንደሌለ በገሃድ አይቶታል።ከገንጣዮችና ከመገንጠል ቢለያይ የሚቀርበት ክልል የተባለ እስርቤትና ሰንሰለት ብቻ ነው። የሚያተርፈው ግን በገንዘብ የማይተመን የትልቅ አገር ባለቤትና በነጻ በሚፈልገው ቦታ ተንቀሳቅሶ የመኖር መብትና ነጻነቱን ነው።

ወያኔ ከባዕዳን መንግሥት ጋር የሚያደርገው መቀራረብና የሚፈራረመው ውል ለመሪዎቹና የባዕዳኑን ጥቅምና ፍላጎት ለማስከበር፣ብዙሃኑን ለባዕዳን መሣሪያ ለማድረግ እንጂ የሚጠቅም አይደለም።እስከ አሁንም ድረስ ልጆቹን ገብሮ ያገኘው ጉዳት እንጂ ጥቅም የለም።አሁንም ከባዕዳን አገሮች ይበልጥ ባርነትን እንጂ ነጻነትን አይቀዳጅም።የራሱ የሆነችው አገር፣ የኢትዮጵያ ባለቤት ለመሆን በሚያስችለው የጋራ ትግል ውስጥ ቢሰለፍ የተከበረና የሚፈራ ሕዝብ ይሆናል። የባዕዳኑ ጣልቃ ገብነት እንዲያም እንዳይሆንና ለዚያ ትልቅነት እንዳይበቃ ነው።

ሌላው የሰሞኑ ክስተት በደቡብ ክልል በተለይም ጉጂ በተባለው አካባቢ በሚኖሩ የጉጂ ማህበረሰቦችና በኦሮሞ ተናጋሪ ማህበረሰቦች መካከል በተፈጠረው ግጭት የብዙ ሰዎች ህይወት መጥፋቱ ነው።ይህ ግጭት የሚያሳዬው ቢኖር ወደፊትም ቢሆን በሁለቱ ማህበረሰቦች መካከል በመዋጥና ባለመዋጥ ምክንያት ግጭትና ጦርነት ሊኖር እንደሚችል ነው።ተመሳሳይ ግጭቶችም በዬቦታው ተከስተዋል። በአማራው ላይ የሚደርሰው ያላባራ ጭፍጨፋም በኦሮሚያና በቤንሻንጉል ውስጥ በስፋት ቀጥሏል። የጎሰኞች ስርዓት እስካለ ድረስ ማንኛውም ማህበረሰብ በሰላም እንደማይኖር ግልጽ ነው።መታወቅ ያለበት አንዱ ሞቶ ገዳዩ ብቻውን በሰላም የሚኖርበት ዕድል እንደማይኖር ነው።ለሁሉም ተመሳሳይና ተመጣጣኝ ምላሽ እንደሚኖር በሳይንስ ተረጋግጧል።

የሕዝብ ትግል ሲበረታ የጠላት አቅምና ሞራል እዬፈሰሰ ለሕዝብ ፍላጎት እጅ መስጠቱ የማይካድ ሃቅ ነው።ሰሞኑንም ያዬነው ይህንን ያረጋግጣል።ከመንገድ ላይ አፍኖ የወሰደው ጀነራል ተፈራ ማሞን ካለፍርድ ሂደት በነጻ መልቀቁ የሕዝቡ ትግል ውጤት ነው ብለን እናምናለን።የጀነራሉን ያለፈ ታሪክና አቋም ስንፈትሽ ለመንግሥት ፍላጎት እጁን ሰጥቶ ፣ለመተባበርና ድምጹን አጥፍቶ ለመኖር ተስማምቶ እንዳልሆነ እናምናለን።በመንግሥት ዳረጎት አቋማቸውን የሚለውጡ መኖራቸውን ብናውቅም ከሁለት ቀን በፊት በኢትዮ360 ስርጭት ስለ ጀነራል ከማል ገልቹ የወጣው መረጃ ባያስደነግጥም ምን ያህል ዓላማ ቢስነት ለጥቅም የሚገዙበት ድክመት እንደሆነ ለማዬት ችለናል።ጀነራሉ መንግሥትን በማጋለጥ ለጥቂት ጊዜ ውርውር ካለ በኋላ ሳይታሰብ ድምጹን ማጥፋቱና የመሰወሩ ምስጢር ሲገለጥ አብይ አህመድ አባሳንጆን ይዞ የተዝናናበት የባሌ እርሻ መሬት ለገማል ገልቹ በተሰጠው ትራክተርና መሬት የለማ መሆኑን ለመስማት በቅተናል።ዕድሜ ከሰጠን የሌሎቹም ከሃዲና እራስ ወዳዶች ታሪክ የምንሰማበት ጊዜ እሩቅ አይሆንም።

በመጨረሻም ልናሳስብ የምንወደው የአገራችን እጣ ፈንታ የሚወሰነው አገር ወዳዱ በሚያካሂደው የተቀናጀና በጋራ ማዕከል በሚመራ ትግሉ ስለሆነ በዬቦታው የተበታተነው ሕዝባዊ እምቢባይነትና የፋኖ ትግል በአንድ ድርጅታዊ አመራር ሥር እንዲሆን ነው።በግለሰብና በነጠላ ድርጅት ባለቤትነትና ቁጥጥር ሳይወድቅ ሁሉም በሚሳተፍበት የጋራ ተቋም ቢመራ ለትግሉ ዋስትና ይኖረዋል።ድርጅት ወይም ግለሰብ ቢሞት ወይም ቢያፈነግጥ ትግሉ ሊሞትና ሊኮላሽ አይችልም።

በዬቦታው የተቋቋሙት የድጋፍ ኮሚቴዎችም በቡድን ተበታትነው ከሚጮሁና እርዳታ ከሚሰበስቡ በጥምረት አንድ የእርዳታ ማእከል ቢፈጥሩ ድካማቸው ትርጉም ይኖረዋል።ከብክነትም ይድናል።በአገር ቤቱ ትግል ፋኖ በሚለው ስያሜ ሁሉም ቢጠቃለል፣የውጩም የፋኖ ድጋፍ ሰብሳቢ ግብረሃይል ተብሎ አንድ አመራር ቢኖረው፣የገንዘብ ማሰባሰቢያው የባንክ ቁጥርም አንድ ቢሆን የሁሉንም አመኔታ ያገኛልለቁጥጥር ያመቻል፤፣ውጤቱም ያማረ ይሆናል።ስለሆነም በዬቦታው የምትንቀሳቀሱ በአንድ ጣራ ስር ተሰባሰቡ እንላለን።

ሌላው የአማራው ማህበረሰብ ሕዝባዊ ትግል የአማራጭ ዓላማዎችን ነድፎ መጓዝ እንዳለበት ለማስታወስ እንወዳለን።እራሱን በማዳኑና ኢትዮጵያን በማዳኑ ትግል ዙሪያ ሊከሰቱ የሚችሉትን እንቅፋቶች በማጤን ሊቋቋም የሚችልበትን ስልት ይዞ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ አለበት እንላለን። ኢትዮጵያ ዱሮም በትልቅነት አሁንም ባለችበት ደረጃ ኖራለች ወደፊትም እንደትግሉ ውጤት መኖሯ አይቀርምና ለዚያ ተመጣጣኝ የሆነ የፖለቲካ፣የኤኮኖሚና፣የማህበረሰብአዊ ዝግጅት ማድረጉ ግዴታ ነው።ኢትዮጵያ ኢትዮጵያውያን ባሉበት ሁሉ ትኖራለች፤ሰንደቅ ዓላማዋም ሲውለበለብ ይኖራል።

በመጨረሻ ላይ ልንጠቁም የምንወደው በሁሉም አቅጣጫ የሽግግር መንግሥት ይቋቋም የሚለው ጥያቄ የእኛም ጥያቄ መሆኑን ሲሆን የእኛ የሽግግር መንግሥት ሌሎቹ ሁሉም የሚሳተፍበት ከሚሉት

ቅርጸቢስ የተለዩ መሆኑን ነው።እኛ የሽግግር መንግሥት ስንል የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ የሚካተቱበት መንግሥት ማለታችን ነው እንጂ አሰሱ ገሰሱ የሚጠቀጠቅበት ቅርጽና ዓላማ ቢስ የሆነ ስብስብ የሚተራመስበት መንግሥት ማለታችን አይደለም።የእኛ የሽግግር መንግሥት ስንል የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት።

1 በኢትዮጵያዊነት ማመን፣በረጅም ታሪኳ የሚኮራ፣መግለጫዋ የሆነውን ሰንደቅዓላማዋን የሚያከብርና የሚያስከብር

2 የጎሳ ፖለቲካንና የክልል አወቃቀርን ከነ ሕገ ጎሳው ለማሶገድ የቆረጠ፤የሃይማኖት አድልኦ የሌለው፣ ለፍትሕና ለእኩልነት የቆመ

3 የኢትዮጵያን አንድነትና ዳር ድንበር ለማስከበር የጸና አቋም ያለው፣ለባዕዳን ያላጎበደደ

እነዚህ ከብዙ በጥቂቱ ለሽግግር መንግሥቱ መመዘኛዎች ይረዳሉ ፣ከግሳንግስ ስብስብነትና ሊያስከትል ከሚችለው የእርስ በርስ ጭቅጭቅና ዓላማ ቢስ ንትርክ ያድናሉ እንላለን።

ሁሉም ፋኖ ይሁን!በአንድ ጣራ ስር ይሰለፍ!!ለሕዝባዊ ትግሉ የሚችለውን ያበርክት!!!

ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘለዓለም ትኑር!!!!